**SIDAAMU DAGOOMU QOQQOWI MOOTIMMA AFFINI GAAZEEXA**

**የሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት አፍኒ ጋዜጣ**

**SIDAAMA NATIONAL REGIONAL STATE AFFINI GAZETA**

| | | |
|---|---|---|
| 1ki Diro Kiiro 15<br>Hawaasa, Dotteessa 15, 2013 M.D | Sidaamu Dagoomu Qoqqowi Mootimma Amaalete Mini Allaalshi Hundanni Fulinoho<br>በሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ | ፩ኛ ዓመት ቁጥር ፲፭<br>ሀዋሳ ሚያዝያ ፲፭ ቀን ፳፻፲፫ ዓ.ም |


**Amado**

**Lallawu Kiiro 15/2013**

**Sidaamu Dagoomu Qoqqowu Mootimma Fayyimmate Owaante Uynanni Garanna Gashshootu Lallawa …… Qoola ….**

**ማውጫ**

**አዋጅ ቁጥር ፲፭/፳፻፲፫**

**የሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የጤና አገልግሎት አሰጣጥና አስተዳደር አዋጅ …… ገጽ ….**


## LALLAWU KIIRO 15/2013

## Sidaamu Dagoomu Qoqqowu Mootimma Fayyimmate Owaante Uynanni Garanna Gashshootu Lallawa

Sidaamu Dagoomu Qoqqowu Mootimma giddo fayyimmate owaante uynanni gari deerrasi agadhinohanna amanyootunni massanganniha ikkanno gede assiisate babbaxxino dirimira afantanno fayyimmate uurrinshuwa bilchaattino: massagate, loosatenna harunsate amanyootinni massagantanno gede assate hasiisannoha ikke afamasinni;

Fayyimmate uurrinshuwata owaantete

## አዋጅ ቁጥር ፲፭/፳፻፲፫

## የሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የጤና አገልግሎት አሰጣጥና አስተዳደር አዋጅ

የሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የጤና አገልግሎት አሰጣጥ ደረጃውን የጠበቀ እና በሥርዓት የሚመራ እንዲሆን ለማስቻል በተለያዩ ደረጃ የሚገኙ የጤና ተቋማት ወጥ በሆነ የአመራር፣ የአሠራርና የክትትል ሥርዓት እንዲመሩ ማድረግ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

የጤና ተቋማት የአገልግሎት ጥራትና ብቃት

silanchimmanna ikkadimma kaajjishate loosate amanyoote diriirsatenni haaro kalaqamanno dhibbira hasiissanno balaxote qoropho, wiinamu tumonna konneno gargadhate kaa'lanno mashalaqqete amanyootinna dhuku hee'rannosi gede assate hasiisannoha ikke afamasinni;

Kalqoomunna gobbomu deerrinni assinoonni soorronna galo assootuwa soorramanni kainohunni fayyimmate owaante uytanno uurrinshuwa: tantano, loosu massago, hattono fayyimmate owaante iillisho lexxitanni daasenninna konni ledo amadisiise wiinamino garinni soorramannohunni baatooshshu amanyooti ledo taashsha hasiissannota ikkite afamasenni;

Dagoomu fayyimma aana gawajjo iillishanno dhibba ajishate baatooshshiweelo uynanni fayyimmate owaante halashsha hasiisasinni;

Yanna xa'mitannota yannitte xagishsha uynanni fayyimmate uurrinshuwa heedhanno gede dandiissiisatenni silancho ikkitino fayyimmate owaante baalaho iillitanno garinni suffanno gede hattono kakkadiishshanna hedeweelcho dano ikkadimmatenni gargarranni fayyimmate amanyooti hee'ranno gede dandiissiisatenni massagaanote qeecha dhaabbachisha hasiisasinni;

Sidaamu Dagoomu Qoqqowu Mootimma Bayriidi Seeri quwa 48 cinaancho quwa 3 fidale (a) garinni aane nooha lallamboonni.

ለማጠናከር የአሰራር ስርዓቶችን በመዘርጋት አዲስ ስለሚከሰቱ በሽታዎች ተገቢውን ቅድመ ጥንቃቄ፣ አፋጣኝ ምላሽና ለዚሁ የሚሆን የመረጃ ሥርዓትና አቅም እንዲኖር ማስቻል አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

በዓለም አቀፍና በሀገር አቀፍ ደረጃ በተደረጉ ለውጦችና ነባራዊ ሁኔታዎች መቀያየር የተነሳ የጤና አገልግሎት መስጫ ተቋማት አደረጃጀት፣ የሥራ አመራር እንዲሁም የጤና አገልግሎት ሽፋን እያደገ በመምጣቱ እና ከዚሁ ጋር ተያይዞ በፈጣን ሁኔታ ከሚለዋወጠው የክፍያ ሥርዓት ጋር ማጣጣም አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

በህብረተሰብ ጤና ላይ ጉዳት የሚያደርሱ በሽታዎችን ለመቀነስ ያለክፍያ የሚሰጡ የጤና አገልግሎቶችን ማስፋት በማስፈለጉ፤

ወቅቱን የሚመጥን ዘመናዊ ህክምና የሚሰጡ ጤና ተቋማት እንዲኖሩ በማስቻል ጥራት ያለው የጤና አገልግሎት በፍትሀዊነት እንዲቀጥል እንዲሁም ለወረርሽኝ እና ለድንገተኛ አደጋዎች የማይበገር የጤና ሥርዓት እንዲኖር በማስቻል የአመራሩን ሚና ማሳደግ በማስፈለጉ፤

በሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፵፰ ንዑስ አንቀጽ ፫ ፊደል ተራ (ሀ) መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

## GAFA MITE

## XAPHOOMA WORO

**1. Harancho Su'ma**

Konne lallawa ‘‘Sidaamu Dagoomu Qoqqowu Mootimma Fayyimmate Owaante Uynanni Garanna Gashshootu Lallawa kiiro 15/2013’’ yine su'minara dandiinanni.

**2. Tiro**

Qaalu horo wole tiro anno gede assa hoogguro konni lallawi giddo:

1. “Qoqqowu Mootimma” yaa Sidaamu Dagoomu Qoqqowu Mootimmati;
2. “Fayyimmate Biiro” yaa Sidaamu Dagoomu Qoqqowu Mootimma Fayyimmate Biiroti;
3. “Hosipitaalete Looso Massagaano Boorde” yaa mootimmate hospitaale giddo babbaxxitino hajo laánnonsa mootimmate bissanna dagoomu riqiwamaano miiloomimmatenni hanqaffannota ikkite uurrinshannita xaphooma loosu massago mixonna baajeette aliidimmatenni murannonna massaganno bisooti;
4. “Umi Dirimi Fayyimmate Awuutishshi Mereerishi Looso Massagaano Boorde” babbaxxitino hajo laánnonsa mootimmate bissanna dagoomu riqiwamaano miiloomimmatenni hanqaffannota ikkite umi dirimi fayyimmate awuutishshi mittimmata xaphooma loosu massagaano mixonna

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

**፩ አጭር ርዕስ**

ይህ አዋጅ “የሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የጤና አገልግሎት አሰጣጥና አስተዳደር አዋጅ ቁጥር ፲፭/፳፻፲፫” ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

**፪ ትርጓሜ**

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጥ ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፡-

፩ “ክልል መንግሥት” ማለት የሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ነው፤

፪ “ቢሮ” ማለት የሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የጤና ቢሮ ነው፤

፫ “የሆስፒታል የሥራ አመራር ቦርድ” ማለት በመንግሥት ሆስፒታል ከተለያዩ አግባብነት ካላቸው የመንግሥት አካላት እና የማህበረሰብ ተወካይ በአባልነት የሚያቅፍ ሆኖ የተቋሙን አጠቃላይ የሥራ አመራር ዕቅድና በጀት በበላይነት የሚወስንና የሚመራ አካል ነው፤

፬ “የመጀመርያ ደረጃ የጤና ክብካቤ አሃድ የሥራ አመራር ቦርድ” ማለት ከተለያዩ አግባብነት ካላቸው የመንግስት አካላት እና የማህበረሰብ ተወካይ በአባልነት የሚያቅፍ ሆኖ የመጀመርያ ደረጃ የጤና ክብካቤ አሃዱን አጠቃላይ የሥራ አመራር እቅድና

baajeette aliidimmatenni murannonna massaganno bisooti;

5. “Hospitaalete Looso Massagaano Komite” yaa mootimmate hospitaale giddo babbaxxitino loosu handaarranni fultino miilla noota ikkite hospitaalenniha barru barrunku loosu millimmo aliidimmatenni massagannonna harunsanno bisooti;
6. “Umi Dirimi Fayyimmate Awuutishshi Mereerishi Looso Massagaano Komite” yaa umi dirimi fayyimmate awuutishshi mittimma babbaxxitino loosu handaarranni fultino miilla noota ikkite hospitaalenniha barru barrunku loosu millimmo aliidimmatenni massaggannonna harunsanno;
7. “Mootimmate Fayyimmate Uurrinsha” yaa qoqqowu mootimma hunda galtanno hospitaallanna umi dirimi fayyimmate awuutishshi mereershuwaati;
8. “Hallanyu Fayyimmate Uurrinsha” yaa fayyimmate handaarinni mootimmate tantano gobbaanni hallanyunni fayyimmate owaante uytanno gede fajjo uynoonninsa uurrinshuwa kamaltanno;
9. “Mootimmaame Ikkitinokki Fayyimmate Uurrinsha” yaa fayyimmate handaarinni mootimmate tantano gobbaanni fayyimmate owaante uytanno gede fajjo uynoonninsa tirfe afi’rate uurritinokki uurrinshaati;
10. “Fayyimmate Owaante” yaa dhibbu gargarooshshenna qorqorsha, fayyimma dhaawate, taraawanno dhibba gaaramate,

በጀት በበላይነት የሚወስንና የሚመራ አካል ነው፤

፭ “የሆስፒታል ሥራ አመራር ኮሚቴ” ማለት በመንግሥት ሆስፒታል አግባብ ካላቸው የስራ ክፍሎች የተውጣጡ አባላት ያሉበት ሆኖ የሆስፒታሉን የዕለት ተዕለት የሥራ እንቅስቃሴ በበላይነት የሚመራና የሚከታተል አካል ነው፤

፮ “የመጀመርያ ደረጃ የጤና ክብካቤ አሃድ የሥራ አመራር ኮሚቴ” ማለት በመጀመርያ ደረጃ የጤና ክብካቤ አሃድ ከተለያዩ የሥራ ክፍሎች የተውጣጡ አባላት ያሉበት ሆኖ የተቋሙን የዕለት ተዕለት የሥራ እንቅስቃሴ በበላይነት የሚመራና የሚከታተል አካል ነው፤

፯ “የመንግሥት ጤና ተቋም” ማለት በክልሉ መንግሥት ሥር የሚተዳደር ሆስፒታልና የመጀመሪያ ደረጃ ጤና ክብካቤ አሀድ ነው፤

፰ “የግል ጤና ተቋም” ማለት በጤና ዘርፍ ከመንግሥት መዋቅር ውጭ በግል የጤና አገልግሎት እንዲሰጥ ፈቃድ የተሰጠው ድርጅትን ያጠቃልላል፤

፱ “መንግሥታዊ ያልሆነ ጤና ተቋም” ማለት በጤና ዘርፍ ከመንግስት መዋቅር ውጭ የጤና አገልግሎት እንዲሰጥ ፈቃድ የተሰጠው ለትርፍ ያልተቋቋመ ነው፤

፲ “የጤና አገልግሎት” ማለት የበሽታ መከላከልንና ቁጥጥርን፣ ጤና

fayyimmate ledo amadantanno xiinxallonna xagishsha kamalanno;

11. “Wiinamu Fayyimmate Owaante” yaa kalaqamunninna mannu loosino dano korinni kalqantanno xissora uynanni fayyimmate owaanteeti;
12. “Kakkadiishsha” yaa hedeweelcho hala’lannonna dhibbunni gawajjantanno manni kiiro kalqete deerri wodhi-worora worroonnihunni aleenni ikkirooti;
13. “Eo” yaa fayyimmate uurrinshara uynanninsa ayeetano: fayyimmate owaante, woloota owaantenninna danunni ikko woxunni afidhanno kaa’looti;
14. “Baatooshshiweelo Fayyimmate Owaante” yaa dagoomunnita fayyimma agadhate gade woyyeessate hattono daga fayyimma agadhate jawa horo noonsa fayyimmate owaante aatenni ledo amadaminohunni baalante dagoomu bissara baatooshshiweelo uynanni owaanteeti;
15. “Qorichishshu Baatooshshe” yaa ayee manchino safote fayyimmate owaante uurrinshanni afi’ra dandaanno owaante sae deerrisi aleenni ikkitino uurrinshara owaatamiro baatanno gede xa’minanni lexxote baatooshsheeti;
16. “Baaxxa Dandiitannokki Dagoomu Bissara Uynanni Xagishshu Owaante” yaa fulo hajo la’annonsa bissa baatteenna baatate anga ajjannonsa dagoomu bissara uynanni fayyimmate owaanteeti;

ማኅልበትን፣ የተላላፊ በሽታዎች ቅኝትን፣ ጤና ነክ ምርመራዎችንና ሕክምናን ያጠቃልላል፤

፲፩ “የአስቸኳይ ጊዜ የጤና አገልግሎት” ማለት በተፈጥሮና በሰው ሰራሽ ክስተቶች ምክንያት ለሚከሰት እክል የሚሰጥ የጤና አገልግሎት ነው፤

፲፪ “ወረርሽኝ” ማለት በድንገት የተስፋፋና በበሽታ የተጠቁ ሰዎች ቁጥር በዓለም አቀፍ መስፈርት ከተቀጠመው በላይ ሲሆን ነው፤

፲፫ “ገቢ” ማለት የጤና ተቋማት ከሚሰጧቸው ማናቸውም የጤና አገልግሎቶች፣ ከሌሎች አገልግሎቶችና በዓይነትም ሆነ በጥሬ ገንዘብ የሚያገኙት እርዳታ ነው፤

፲፬ “ክፍያ የማይጠየቅበት የጤና አገልግሎት” ማለት የኅብረተሰቡን የጤና አጠባበቅ ልምድ ከማሳደግ እንዲሁም በሕዝብ ጤና አጠባበቅ ጉልህ ጠቀሜታ ያላቸውን የጤና አገልግሎቶች ከመስጠት ጋር በተያያዘ ለሁሉም የኅብረተሰብ ክፍል ያለክፍያ የሚሰጥ አገልግሎት ነው፤

፲፭ “የመጣሻ ክፍያ” ማለት ማንኛውም ሰው በመሠረታዊ ጤና አገልግሎት ተቋም ሊያገኝ የሚችለውን አገልግሎት አልፎ ከደረጃው በላይ በሆነ ተቋም ሲገለገል እንዲከፍል የሚጠየቀው ተጨማሪ ክፍያ ነው፤

፲፮ “መክፈል ለማይችሉ የህብረተሰብ ክፍሎች

17. “Fayyimmate Woowe” yaa owaantete horoonsi’raano fulo sayikki garonni baantanni mootimmate woy hallanyu uurrinshaati;
18. “Mancho” yaa kalaqamunni manna ikke kalaqaminoha woy seerunni mannimmate qoosso uynoonnisi bisoti;
19. Konni lallawi giddo mitte koo-teemanni xawinsonnihu wole koo-teemano amadanno.

**3. Lallawu Jeefishshu Mami-geeshsha**

Kuni lallawi aye mootimmate fayyimmate uurrinsha giddo hasiishshu garinni loosu aana hosannoha ikkanno.

**GAFA LAME**

**FAYYIMMATE OWAANTE UYNANNI GARANNA GASHSHOOTE**

**4. Fayyimmate Owaante Uynanni Wodhi-woro**

1. Ayeetino mootimmate fayyimmate uurrinsha owaante uytannohu hajo la’annonsa bissa murtanno baatooshshe baatisiisatenni ikkanno.
2. Konni quwi cinaanchu quwi 1 worroonnihu noo gede hee’reenna ayee manchirano baaxxa hoogasi korinni fayyimmate owaante dihoollannisi.

የሚሰጥ ሕክምና አገልግሎት” ማለት ወጪው አግባብ ባለው አካል ተሸፍኖ የመክፈል አቅም ለሌላቸው የህብረተሰብ ክፍሎች የሚሰጥ የጤና አገልግሎት ነው፤

፲፯ “የጤና መድህን” ማለት የአገልግሎት ተጠቃሚዎችን ወጪ በሦስተኛ ወገን የሚሸፍን የመንግስት ወይም የግል ድርጅት ነው፤

፲፰ “ሰው” ማለት ማንኛውም የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤

፲፱ በዚህ አዋጅ ውስጥ በአንድ ጾታ የተደነገገው ሌላኛውንም ጾታ ያካትታል፡፡

**፫ የአዋጁ የተፈጻሚነት ወሰን**

ይህ አዋጅ በማንኛውም የመንግሥት ጤና ተቋም ውስጥ እንደ አስፈላጊነቱ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

**ክፍል ሁለት**

**የጤና አገልግሎት አሰጣጥና አስተዳደር**

**፬ የጤና አገልግሎት አሰጣጥ መርህ**

፩ ማንኛውም የመንግሥት የጤና ተቋም አገልግሎት የሚሰጠው አግባብ ባለው አካል የሚወሰነውን ክፍያ በማስከፈል ይሆናል፡፡

፪ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ ላይ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም

3. Mootimmaamenna mootimmaame ikkitinokki fayyimmate owaante uytanno uurrinshuwa mixote qixxeessidhanno woyte fayyimmate owaante aate amanyooti aana dagoomu beeqqo buuxisiisa noonsa.
4. Aye fayyimmate uurrinsha balaxote baatooshshe xa’mitukkinni hedeweelcho fayyimmate owaante aate gadacho noonsa.
5. Konni quwi cinaanchu quwi 4 xawinsoonnihu hee’rirono fulo hajo la’annonsa bissanni baatantanno; tittirshu xawishsha wodhotenni murranniha ikkanno.
6. Ayeno fayyimmate owaante aate loosi aana qeecha adhanno ogeessi woy uurrinsha aantesi agarino garinni ogimmate fajjonna fayyimmate uurrinsha ikkadimma buuxishshi fajjo afi’rikkinni fayyimmate owaante aate didandaanno.
7. Fayyimmate keella agurranna ayeetino fayyimmate uurrinsha dagoomaho 24 saate xagishshu owaante aate gadacho noose; loosu aana hosiisate gara wodhotenni murranni.
8. Hallanyu fayyimmate uurrinshuwa baatooshshiweelo uynanni owaantete tittirshi giddonni qara ikkitinore aate gadacho noonsa; may dani dhibbira uytannoro wodhote aana xawinsanni.

ሰው መክፈል ባለመቻሉ ምክንያት የጤና አገልግሎት አይከለከልም፡፡

፫ የመንግሥትና መንግሥታዊ ያልሆኑ ጤና አገልግሎት መስጫ ተቋማት በዕቅድ ዝግጅታቸውና የጤና አገልግሎት አሰጣጥ ላይ የህብረተሰብ ተሳትፎን ማረጋገጥ አለባቸው፡፡

፬ ማንኛውም የጤና ተቋም ቅድመ ክፍያ ሳይጠይቅ ድንገተኛ የጤና አገልግሎት የመስጠት ግዴታ አለበት፡፡

፭ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፬ የተመለከተው ቢኖርም ወጪው ጉዳዩ በሚመለከተው አካል ይሸፈናል፣ ዝርዝሩ በደንብ ይወሰናል፡፡

፮ ማናቸውም የጤና አገልግሎት በመስጠት ተግባር ላይ የሚሰማራ የጤና ባለሙያ ወይም ተቋም እንደ ቅደም ተከተሉ የሙያ ፍቃድ እና የጤና ተቋም ብቃት ማረጋገጫ ፈቃድ ሳያገኝ የጤና አገልግሎት መስጠት አይችልም፡፡

፯ ጤና ኬላን ሳይጨምር ማንኛውም የጤና ተቋም ለህብረተሰቡ የሃያ አራት ሰዓት የሕክምና አገልግሎት የመስጠት ግዴታ አለበት፣ አፈፃፀሙም በደንብ ይወሰናል፡፡

፰ የግል ጤና ተቋማት ያለክፍያ ከሚሰጡ አገልግሎቶች ዝርዝር ውስጥ የተመረጡትን የመስጠት ግዴታ አለባቸው፤ አይነቶቹ በደንብ ላይ ይገለጻሉ፡፡

**5. Fayyimmate Owaante Tantanonna Gashshootu Bissa**

Fayyimmate Owaante Gashshooti bissa:

1. Fayyimmate Biiro;
2. Hosipitaallate Loosu Massagaano Boorde;
3. Hosipitaallate Loosu Massagaano Komite;
4. Umi Dirimi Fayyimmate Awuutishshi Mereershi Loosu Massagaano Boorde;
5. Umi Dirimi Fayyimmate Awuutishshi Mereershi Loosu Massagaano Komiteeti.

**6. Biirote Biilloonyenna Loosu Qeecha**

Biirote woloota seeruwanni uyinoonnise biilloonyinna loosu qeechi noo gedeenni hee'reenna aane noo biilloonyinna loosu qeechi hee'rannose:

1. Fayyimmate uurrinshuwa heedhansara hasiissannota mannu wolqa batinye, ikkadimmanna fayyimmannita duuchu ragi ogimma, ijaare, xagishshu udiinnenna owaante uynanni deerra murtanno.
2. Mootimmate fayyimmate uurrinshuwa uytanno fayyimmate owaantera baantansara hasiisanno baatooshshi uurrinshuwate fulonna daga baaxxate dhuki hedote giddo woramasi deerru deerrunku heedhanno boordenni xiinxallante shiqqino murote hedo keente gumultanno; loosu aana hosase garano harunsitanno.
3. Mootimmate fayyimmate owaante uytanno uurrinshuwa: mannu wolqa ikkadimma, loosu

**፭ የጤና አገልግሎት አደረጃጀትና አስተዳደር አካላት**

የጤና አገልግሎት የአስተዳደር አካላት፡-

፩ የጤና ቢሮ፤

፪ የሆስፒታሎች የሥራ አመራር ቦርድ፤

፫ የሆስፒታሎች የሥራ አመራር ኮሚቴ፤

፬ የመጀመርያ ደረጃ የጤና ክብካቤ አሃድ የሥራ አመራር ቦርድ፤

፭ የመጀመርያ ደረጃ የጤና ክብካቤ አሃድ የሥራ አመራር ኮሚቴ ናቸው።

**፮ የቢሮ ሥልጣንና ተግባር**

ቢሮው በሌሎች ሕጎች የተሰጠው ሥልጣንና ተግባር እንደተጠበቀ ሆኖ የሚከተሉ ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል።

፩ የጤና ተቋማት ሊኖራቸው የሚገባውን የሰው ኃይል ብዛት፣ ብቃትና የሙያ ስብጥር፣ የሕንጻ፣ የሕክምና መሣሪያዎች እና የመገልገያዎች ደረጃ ይወስናል።

፪ የመንግሥት ጤና ተቋማት ለሚሰጡት የጤና አገልግሎት ሊከፈል የሚገባውን ክፍያ የተቋማቱን ወጪ እና የሕዝቡን የመክፈል አቅም ከግምት ውስጥ ማስገባቱን በየደረጃው ባለው ቦርድ ተጠንቶ የቀረበለትን የውሳኔ ሃሳብ መርምሮ ያፀድቃል፣ አፈፃፀሙን ይከታተላል።

፫ የመንግሥት የጤና አገልግሎት መስጫ ተቋማት የሰው ኃይል ብቃት፣ የአሰራር

amanyootenna gumulsiisate dhuki jawaata ikkanno gede hasiissanno irko assitanno.

4. Fayyimmate uurrinshuwa deerra badate dandiissiisanno keenishshu amanyoote diriirsitanno; deerra uytanno.
5. Ayeetino fayyimmate uurrinshuwa deerrase agadhitino owaante uytanni noo gede harunsitanno; qorqortanno.
6. Fayyimmate owaante halashshatenna silanchimma woyyeessate fultanno addi addi seeruwa loosu aana hosansa harunsitanno; qorqortanno.
7. Ayeeno fayyimmate ogeessihu woy uurrinshahu ogimmate amanyooti agaramasi harunsitanno; qorqortanno; xe’nenna foonqe leelturo qaafo adhitanno; tittirshu xawishsha wodhete aana murranniha ikkanno.
8. Hallanyunna woloota mootimmaame ikkitinokki fayyimmate handaarinni loossanno uurrinshuwa ledo fayyimmate uurrinshuwa hala’litannonna owaantete silanchimma woyyaabbanno gede tekinikete irko assitanno.
9. Qixxaabbanno qajeelshuwatenna loosu biddissuwa aana hallanyu handaarra beeqqitanno gede assitanno.
10. Babbaxxino deerrira afantanno fayyimmate owaante massagaano bissanna fayyimmate uurrinshuwa dano iillitara albaanni gargaratenna qorqorate dandiissiissanno mashalaqqetenna *loojistikete* dhuki bilchaata ikkanno gede hattono balaxi-agadhote hasiisannore injeessinanni gede assitanno.

ሥርዓት እና የማስፈጸም አቅም እንዲጠናከር ተገቢውን እገዛ ያደርጋል፡፡

፬ የጤና ተቋማትን ደረጃ መለየት የሚያስችል የመመዘኛ ሥርዓት ይዘረጋል፣ ደረጃ ይሰጣል፡፡

፭ ማናቸውም የጤና ተቋማት ደረጃውን የጠበቀ አገልግሎት እየሰጡ ስለመሆናቸው ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፡፡

፮ የጤና አገልግሎት ለማስፋፋትና ጥራቱንም ለማሻሻል የወጡ ልዩ ልዩ ህጎች በሥራ ላይ መዋላቸውን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፡፡

፯ ማንኛውም የጤና ባለሙያ ወይም ተቋም የሙያ ሥነ ምግባር መጠበቁን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፣ የማይፈጸም ሲሆን እርምጃ ይወስዳል፣ ዝርዝሩ በደንብ ይወሰናል፡፡

፰ ከግሉና ሌሎች መንግሥታዊ ካልሆኑ በጤና ዘርፍ ከሚሠሩ ድርጅቶች ጋር የጤና ተቋማት እንዲስፋፉና የአገልግሎት ጥራት እንዲሻሻል የቴክኒክ እገዛ ያደርጋል፡፡

፱ በሚዘጋጁ የሥልጠናና የአሰራር መመሪያዎች ላይ የግሉ ዘርፍ እንዲሳተፍ ያደርጋል፡፡

፲ በተለያዩ ደረጃ የሚገኙ የጤና አገልግሎት የአመራር አካላትና የጤና ድርጅቶች አደጋ ከመድረሱ በፊት ለመከላከልና ለመቆጣጠር የሚያስችል የመረጃና የሎጂሲቲክ አቅም

11. Kalaqantanno kakkadiishshanna woloota dhibbu dani taje gamba assitanno; fatilsitanno; murtanno; tuqissanno.
12. Konni quwi cinaanchu quwi 1-11 xawinsoonnihu noo gede hee’reenna biiro uynoonninsa biilloonye hundaseenni afantanno gashshootu dirimmaranna hajo la’annonsa bissara wo’ma ikko darate uytara dandiitanno.

**7. Hosipitaallate Looso Massagaano Boorde**

1. Mitte mittenti mootimmate hosipitaalla loosu massagaano boordenni massagantanno.
2. Loosu massagaano boorde tantano hospitaalete deerri garinni muramannoha ikkanno. Tittirshu xawishshi wodhotenni muramanno.
3. Hosipitaallate loosu massagaano boorde miilla: somamate gari, loosu dilaalunna qeechu wodhotenni muramanno.

**8. Umi Dirimi Fayyimmate Awuutishshi Mereershi Looso Massagaano Boorde**

1. Umi dirimi fayyimmate awuutishshi mittimma loosu massagaano boorde horoonsi’raano dagoomininnina babbaxxitino mootimmate bissanni fultino waaxo bissanni tantanantannoha ikkanno.
2. Boordete miilla batinyi, loosu dilaalunna qeechu hattono xa’mamaanchimma wodhotenni murantanno.

እንዲገነቡ እንዲሁም የመጠባበቂያ ግብአቶች እንዲመቻቹ ያደርጋል።

፲፩ የሚከሰቱ የወረርሽኝ እና ሌሎች የበሽታ ዓይነቶችን መረጃ ያሰባስባል፣ ይተነትናል፣ ይወስናል፣ ያሠራጫል።

፲፪ በዚህ አንቀጽ ከንዑስ አንቀጽ ፩-፲፩ የተገለጸው እንደተጠበቀ ሆኖ ቢሮው የተሰጠውን ስልጣን በስሩ ለሚገኙ የአስተዳደር እርከኖች እና አግባብነት ላላቸው አካላት በሙሉም ሆነ በከፊል ሊሰጥ ይችላል።

**፯ የሆስፒታሎች የሥራ አመራር ቦርድ**

፩ እያንዳንዱ የመንግሥት ሆስፒታል በሥራ አመራር ቦርድ ይመራል።

፪ የሥራ አመራር ቦርድ አወቃቀር እንደ ሆስፒታሉ ደረጃ የሚወሰን ይሆናል። ዝርዝሩ በደንብ ይወሰናል።

፫ የሆስፒታሎችና የሥራ አመራር ቦርድ አባላት አሰያየም፣ የሥራ ድርሻና ኃላፊነት በደንብ ይወሰናል።

**፰ የመጀመሪያ ደረጃ የጤና ክብካቤ አሃድ የሥራ አመራር ቦርድ**

፩ የመጀመያ ደረጃ የጤና ክብካቤ አሃድ የስራ አመራር ቦርድ ከተጠቃሚ ህብረተሰብና ከተለያዩ የመንግስት አካላት በተውጣጡ ጥምር አካላት የሚዋቀር ይሆናል።

፪ የቦርዱ አባላት ብዛት፣ የስራ ድርሻና

**9. Fayyimmate Uuurrinshuwa Looso Massagaano Komite**

Fayyimmate Uurrinshuwa loosu massagaano komite loosinna qeechi tittirshu xawishshi wodhotenni muramanno.

## GAFA SASE

## FAYYIMMATE OWAANTE UYNANNI AMURAATE

**10. Ogimmate Akatoomme**

Ayeehuno fayyimmate ogeessinna uurrinsha ogimmate akatoomme safote wodhi-woro ayirrisate gadacho noosi.

**11. Dhiwamaano Haa'ratenna Sowate Amanyoote**

1. Ayeehuno fayyimmate ogeessinna uurrinsha deerrisinni agarranni fayyimmate owaante aa noosi.
2. Fayyimmate owaante horoonsi'raano hasidhanno owaantete daninna horoonshu fayyimmate owaante tantano harunsinoha ikkanno. Tittirshu xawishshi wodhotenni muramanno.
3. Dhiwamaano mitte fayyimmate uurrinshanni wole fayyimmate uurrinsha sonkanni woyte dhiwamaano sonkanni gari amanyoote harunsinoha ikka noosi.
4. Dhiwamaano, dhiwamaano haa'rate amanyoote harunsa hoogguro qorichishshu

ኃላፊነት እንዲሁም ተጠያቂነት በደንብ ይወሰናል፡፡

**፱ የጤና ተቋማት የስራ አመራር ኮሚቴ**

የጤና ተቋማት ስራ አመራር ኮሚቴ ዝርዝር ተግባርና ኃላፊት በደንብ ይወሰናል፡፡

## ክፍል ሦስት

## የጤና አገልግሎት የሚሰጥበት አኳሄን

**፲ የሙያ ሥነ-ምግባር**

ማንኛውም የጤና ባለሙያ እና ድርጅት የሙያ ሥነ-ምግባር መርሆዎችን የማክበር ግዴታ አለበት፡፡

**፲፩ የሕሙማን አቀባበልና አላላክ ሥርዓት**

፩ ማንኛውም የጤና ባለሙያ እና ተቋም በደረጃው ሚጠበቀውን የጤና አገልግሎት መስጠት አለበት፡፡

፪ የጤና አገልግሎት ተጠቃሚዎች የሚፈልጉት የአገልግሎት ዓይነትና አጠቃቀም የጤና አገልግሎቱን አደረጃጀት የተከተለ ይሆናል፡፡ ዝርዝሩ በደንብ ይወሰናል፡፡

፫ ሕሙማን ከአንድ ጤና ተቋም ወደሌላ ጤና ተቋም ሲላኩ የህሙማን የአላላክ ስርአትን የተከተለ ይሆናል፡፡

፬ ሕሙማን የቅብብሎሽ ሥርዓትን ካልተከተሉ የመጣሻ ክፍያ እንዲከፍሉ ይደረጋል፡፡

baatooshshe baattanno gede assinanni.

**12. Hallanyu Xagishsha Uynanni Kifile**

1. Hosipitaalla hosipitaalete mitto biso ikkite loossanno hallanyu xagishsha uynanni kifile uurrisidhara dandiitanno.
2. Hallanyu xagishsha uynanni kifile massagate loosonna gashshoote lainohunni tittirshu xawishshi wodhotenni muramanno.

**GAFA SHOOLE**

**BAAXXAA DANDIITANNOKKI DAGOOMU BISSARA XAGISHSHU OWAANTE UYNANNI GARANNA BAATOOSHSHE XA'MINANNIKKI FAYYIMMATE OWAANTE**

**13. Baaxxa Dandiitannokki Dagoomu Bissara Xagishshu Owaante**

1. Baaxxate anga ajjinonsare ikkansa hajo la'annonsa mootimmate bissa uytanno taje shiqishidhanno qaansooti qooxeessinsara afantanno mootimmate fayyimmate owaante uynanni uurrinshuwanni xagishshu owaante afi'rate dandiitanno.
2. Baaxxa dandiitannokki dagoomu bissara xagishshu owaante uynanni amanyooti horoonsi'raano badate ha'rinshonna fulo hiittto riqimbanniro tittirshu xawishshi wodhotenni muramanno.
3. Konni quwi cinaanchu quwi 2 xawinsoonnihu noo gede hee'reenna baaxxa dandiitannokki

**፲፪ የግል ሕክምና መስጫ ክፍል**

፩ ሆስፒታሎች የሆስፒታሉ አንድ አካል ሆኖ የሚሠራ የግል ሕክምና መስጫ ክፍል ሊያቋቁሙ ይችላሉ፡፡

፪ የግል ሕክምና መሰጫ ክፍል አመራር አሠራርና አስተዳደርን በሚመለከት ዝርዝሩ በደንብ ይወሰናል፡፡

**ክፍል አራት**

**መክፈል የማይችሉ የህብረተሰብ ክፍሎች ሕክምና አገልግሎት አሰጣጥ እና ክፍያ የማይጠየቅባቸው የጤና አገልግሎቶች**

**፲፫ መክፈል የማይችሉ ህብረተሰብ ክፍሎች ሕክምና አገልግሎት**

፩ የመክፈል አቅም የሌላቸው ስለመሆኑ አግባብ ካለው የመንግሰት አካል የሚሰጥ ማስረጃ የሚያቀርቡ ዜጎች በአቅራቢያቸው በሚገኙ የመንግሥት የጤና አገልግሎት መስጫ ተቋማት የህክምና አገልግሎት ሊያገኙ ይችላሉ፤

፪ መክፈል ለማይችሉ ህብረተሰብ ክፍሎች ሕክምና አገልግሎት የሚሰጥበት ሥርዓት፣ ተጠቃሚዎች የሚለዩበት ሂደትና ወጪው እንዴት እንደሚሸፈን ዝርዝሩ በደንብ ይወሰናል፡፡

፫ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፪ ላይ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ መክፈል

dagoomu bissara xagishshu owaantera hasiissanno diru baajeette giddonni xibbunni 70% (lamalaa anga) qoqqowunna 30% (sajjo anga) woradunni woy quchumu gashshootinni baantanniha ikkanno.

**14. Baatooshshe Xa'minannikki Fayyimmate Owaante**

Mootimmate fayyimmate uurrinshuwa giddo baatooshshiweelo uynanni owaante aante noore ikkitanno.

1. Maatete mixo owaante;
2. Balaxi-ilate, ilatenna ilate-gedensiidi owaante;
3. Amuwunna qaaqquullu *kittiwaate;*
4. *Festullu* xagishsha;
5. Gadache Seyatate korinni uynanni owaante;
6. HIV/AIDS/ amaale, laishshanna xagishsha hattono amatenni godowihura taraawanno HIV/AIDS/ gargarate owaante;
7. Shombu/TB/ dhibbi xagishshi owaante;
8. Mannimmate giddooydi dhibbi xagishsha;
9. Fayyimmate ogeeyye loosu qamatte bidhatto shotissanno *kittiwaatenna* xagishshanna owaante;
10. Kakkadiishshu qorqorsha;
11. Seerunni fajjantinonna hobbaate buuxantino godowa uurrisate xagishsha, hobbaatu mitiimma noo godowa uurrisatenni aanchine uynanni xagishshu owaantenna harunso;
12. Otoottote birxe kaansere *kittiwaatenna* xagishsha;

ለማይችሉ የሕብረተሰብ ክፍሎች ሕክምና አገልግሎት ከሚያስፈልገው ዓመታዊ በጀት ውስጥ ፸% (ሰባ ከመቶ) በክልል እና ፴% (ሳላሳ ከመቶ) በወረዳ ወይም ከተማ አስተዳደር የሚሸፈን ይሆናል፡፡

**፲፬ ክፍያ የማይጠየቅባቸው የጤና አገልግሎቶች**

በመንግሥት የጤና ተቋማት ያለክፍያ የሚሰጡ አገልግሎቶች የሚከተሉት ይሆናሉ፡፡

፩ የቤተሰብ ዕቅድ አገልግሎት፤

፪ ቅድመ ወሊድ፣ ወሊድ እና ድህረ ወሊድ አገልግሎት፤

፫ የእናቶችና ህጻናት ክትባት፤

፬ የፊስቱላ ሕክምና፤

፭ የአስገድዶ መደፈርን ተከትሎ የሚሰጥ አገልግሎት፤

፮ የኤች አይ ቪ /ኤድስ የምክር፣ ምርመራና ሕክምና፣ እንዲሁም ከእናት ወደ ፅንስ የሚተላለፍ የኤች አይ ቪ/ኤድስ መከላከል አገልግሎት፤

፯ የቲቢ በሽታ ሕክምና አገልግሎት፤

፰ የስጋ ደዌ ሕክምና፤

፱ ለጤና ባለሙያዎች የሥራ አካባቢን ስጋት የሚያቃልሉ የክትባትና የሕክምና አገልግሎቶች፤

፲ የወረርሽኝ ቁጥጥር፤

፲፩ በሕግ የተፈቀደና ደህንነቱ የተረጋገጠ የጽንስ-ማቋረጥ ህክምና፣ ደህንነቱ ያልተረጋገጠ የጽንስ-ማቋረጥን ተከትሎ

13. Marqu qaaqquulli xagishsha;
14. Dirinsa mittu woroonni ikkino qaaqquulli xagishshanna owaante;
15. Qaaqquullu sagalete hanqatto xagishsha;
16. *Kalazarete* xagishsha;
17. Shufuru xagishshanna owaante;
18. Fulonsa mootimmatenni baantannire ikkite albillicho noo baatooshshe uynanni gede wodhotenni murranni woloota fayyimmate owaante.

## GAFA ONTE

## MOOTIMMATE FAYYIMMATE UURRINSHUWA WOMAASHSHU GASHSHOOTE

### 15. Eote Buicho

Mootimmate fayyimmate uurrinshuwa baajeette buicho:

1. Ityophiyu adhino kalqoomu sumiimme safonni mootimma qeechite gaantanno baajeettenni;
2. Uytanno fayyimmate owaantenni afidhanno eonni;
3. Gobbate giddonna baara widinni danunninna woxunni afidhanno kaa'lonni;
4. Woloota eote buichonni ikkanno.

### 16. Eote Horoonsha Lainohunni

1. Fayyimmate uurrinshuwa afidhanno eo fayyimmate owaante uurrinsha su'minni

የሚሰጥ ህክምና አገልግሎትና ክትትል፤

፲፪ የማህጸን ጫፍ ካንሰር ክትባትና ህክምና፤

፲፫ የጨቅላ ህጻናት ህክምና፤

፲፬ ዕድሜያቸው ከአንድ ዓመት በታች የሆኑ ህፃናት ህክምና አገልግሎት፤

፲፭ የህፃናት የምግብ እጥረት ህክምና፤

፲፮ የካላዛር ሕክምና፤

፲፯ የአባላዘር ህክምና አግልግሎት፤

፲፰ ወጪያቸው በመንግሥት የሚሸፈን ሆኖ ወደፊት ያለ ክፍያ እንዲሰጡ በደንብ የሚወሰኑ ሌሎች ጤና አገልግሎቶች፡፡

## ክፍል አምስት

## የመንግሥት የጤና ተቋማት የፋይናንስ አስተዳደር

### ፲፭ የገቢ ምንጭ

የመንግሥት የጤና ተቋማት የበጀት ምንጭ፡-

፩ ኢትዮጵያ በተቀበለቻቸው ዓለም አቀፍ ስምምነቶች መሰረት ከመንግሥት በጥቅል የሚመደብ በጀት፤

፪ ከሚሰጡት የጤና አገልግሎት የሚያገኙት ገቢ፤

፫ ከአገር ውስጥና ከውጭ አገር በዓይነትና በጥሬ ገንዘብ የሚገኙ እርዳታዎች፤

፬ ሌሎች የገቢ ምንጮች ይሆናል፡፡

### ፲፮ ስለገቢ አጠቃቀም

፩ የጤና ተቋማት የሚያገኙት ገቢ በጤና

fannanni addi *baankete Akawunte* giddo baxxite ofoltanno.

2. Uytanno owaantenni afidhanno eo wo'munni wo'ma qeechine gaammanninsa baajeette aanano lede loosonsa gumulate hajora hosanno.
3. Fayyimmate uurrinshuwa eo gamba assinoonninna horoonsi'noonni gara biilloonyu noonsa mootimmate bissanni *odiite* assinanni.

**17. Fayyimmate Owaante Baatooshshe**

1. Fayyimmate uurrinshuwa loosu massagaano komite fayyimmate owaante baatooshshi bikka murate woy woyyeessate dandiissiissanno xiinxallo hasiishshise garinni xiinxallinanni gede assatenni murote hedo fayyimmate uurrinsha boordera shiqishshanno.
2. Boorde konni quwi cinaanchu quwi 1 garinni xiinxallineenna shiqqino owaantete baatooshshi bikka, dagoomu baaxxate dhukanna fiixoontanno hajubba xiinxallatenninna keenatenni biirote shiqishshe gumulsiissanno.

**18. Hirotenna Jajju Gashshooote**

1. Fayyimmate uurrinshuwa hirotenna jajju gashshoote loosu aana hosanni noo mootimmate seeri garinni gumultannoha ikkanno.
2. Fayyimmate uurrinshuwa fayyimmate ledo

አገልግሎት ተቋሙ ስም በተከፈተ ልዩ የባንክ ሂሣብ ውስጥ ተለይቶ ይቀመጣል፤

፪ ከሚሰጡት አገልግሎት የሚያገኙት ገቢ ሙሉ በሙሉ በጥቅል ከሚመደብላቸው በጀት በተጨማሪ ለሥራዎቻቸው ማስፈጸሚያ ይውላል፤

፫ የጤና ተቋማት ገቢ አሰባሰብና አጠቃቀም ሥልጣን ባለው የመንግሥት አካል ኦዲት ይደረጋል፤

**፲፯ የጤና አገልግሎት ክፍያ**

፩ የጤና ተቋማት የሥራ አመራር ኮሚቴ የጤና አገልግሎት ክፍያ መጠን ለመተመን ወይም ለማሻሻል የሚያስችል ጥናት እንደአስፈላጊነቱ እንዲከናወን በማድረግ የውሣኔ ሀሳብ ለጤና ተቋሙ ቦርድ ያቀርባል፡፡

፪ ቦርዱ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ መሠረት ተጠንቶ የቀረበውን የአገልግሎት ክፍያ መጠን ከህብረተሰቡ የመክፈል አቅም እና ተያያዥነት ካላቸው ጉዳዮች በማጤንና በመገምገም ለቢሮው አቅርቦ ያስጸድቃል፡፡

**፲፰ ግዥና ንብረት አስተዳደር**

፩ የጤና ተቋማት የግዥና ንብረት አስተዳደር አግባብነት ባለው የመንግስት ህግ መሰረት የሚፈፀም ይሆናል፡፡

፪ የጤና ተቋሞች ጤና ነክ ያልሆኑ አገልግሎቶችን አግባብነት ባለው ህግ

amadantinokki owaante loosu aana hosanni noo seeri garinni sheemaatunni aate dandiitanno.

**19. Fayyimmate Woowe Loosu Aana Hosate Gara**

Biiro babbaxxitino mootimmaame, mootimmaame ikkitinokkinna hallanyu uurrinshuwanna dagooma fayyimmate woowera miiloo'mannonna horoonsi'ranno gara injeessitanno.

**GAFA LEE**

**MOOTIMMATE, MOOTIMMAAME IKKITINOKKINNA HALLANYU FAYYIMMATE UURRINSHUWA HANDAARI HALAMME**

**20. Loosu Qarqara Woyyeessa**

Biiro ogimmate hi'richimma bilchaatisatenninna polisetenni, tekiniketenninna loosu ragaanni loosu qarqara injaado assate mootimmaame ikkitinokki uurrinshuwanna hallanyu handaarra ledo qinaabbenna halante loossanno.

**21. Tajete Qinaawo Gara**

1. Mootimmate, mootimmaame ikkitinokkinna hallanyu fayyimmate uurrinshuwa fultanno wodho garinni dhibbu dananna taraawo lainohunni iibbado mashalaqqe soorri'ra noonsa.
2. Ayeetino fayyimmate uurrinsha uytanno owaante lainohunni barrunna yannate taje amadate, qineessatenna hasiisannoha ikkiro

መሰረት በውል መስጠት ይችላሉ፡፡

**፲፱ የጤና መድህን አተገባበር**

ቢሮው የተለያዩ መንግሥታዊ፣ መንግሥታዊ ያልሆኑና የግል ተቋማትና ህብረተሰቡ በጤና መድህን የሚደራጅበትንና የሚጠቀምበትን ሁኔታ ያመቻቻል፡፡

**ክፍል ስድስት**

**የመንግሥት፣ መንግሥታዊ ያልሆኑና የግሉ ጤና ተቋም ዘርፍ ትብብር**

**፳ የሥራ አካባቢን ስለማሻሻል**

ቢሮው የሙያ ሥነ ምግባርን በማስፈንና በፖሊሲ፣ በቴክኒክና በአሰራር ረገድ የስራ አካባቢን ለማሻሻል መንግሥታዊ ካልሆነ ድርጅትና ከግሉ ዘርፍ ጋር በቅንጅት ይሰራል፡፡

**፳፩ መረጃን ስለማጠናከር**

፩ የመንግሥት፣ መንግሥታዊ ያልሆኑና የግል ጤና ተቋማት በሚወጣ ደንብ መሠረት ስለበሽታዎች ዓይነት እና ሥርጭት ወቅታዊ የሆነ የመረጃ ልውውጥ ማድረግ አለባቸው፡፡

፪ ማንኛውም የጤና ተቋም የሚሰጠውን አገልግሎት በሚመለከት ዕለታዊና ወቅታዊ መረጃ የመያዝ፣ የማደራጀትና አስፈላጊ ሲሆን የማስተላለፍ ግዴታ አለበት፡፡

tareessate gadacho noonsa.

## GAFA LAMALA

## WINAAMU YANNA FAYYIMMATE OWAANTE

**22. Mootimmate, Mootimmame Ikkitinokki Uurrinshubbanna Halanyu Fayimmate Owaante Uynanni Kifilera Uynanni Winaamu Yanna Fayyimmate Owaante**

1. Biiro kalaqamunna mannu loosi dano korinni dagate fayyimmanna heeshsho aana iillitanno dano gargarate dandiinanni gede mootimmate, mootimmaame ikkitinokkinna hallanyu fayyimmate uurrinshanna dagoomu halamanno gede kakkaysatenni wiinamu yanna fayyimmate owaante: qineessitanno, halansiissanno, gumulsiissanno, hurunso assitanno.
2. Ayeetino mootimmaame ikkitinokkinna hallanyu fayyimmate uurrinshuwa kakkadiishshunna woloota wiinamu fayyimmate owaante loossa aana beeqqate qoossonna halamate gadacho noonsa.
3. Wiinamu yanna fayyimmate owaante baatishsha horonsi'ranchu baatanno gede diagarranni.

## ክፍል ሰባት

## የአስቸኳይ ጊዜ የጤና አገልግሎት

**፳፪ በመንግሥት፣ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችና በግል የጤና አገልግሎት መስጫ ተቋማት የሚሰጥ የአስቸኳይ ጊዜ የጤና አገልግሎት**

፩ ቢሮው በተፈጥሮና በሰው ሠራሽ ክስተቶች ምክንያት በሕዝብ ጤናና ሕይወት ላይ የሚደርሰውን አደጋ ለመከላከል እንዲቻል የመንግሥትን፣ መንግሥታዊ ያልሆኑ፣ የግል ጤና ተቋማትን እና ሕህረተሰቡን በማስተባበር የአስቸኳይ ጊዜ የጤና አገልግሎቶችን ያደራጃል፣ ያስተባብራል፣ ያስፈጽማል፣ ክትትል ያደርጋል።

፪ ማንኛውም መንግሥታዊ ያልሆኑና የግል ጤና ተቋማት በወረርሽኝ እና ሌሎች አስቸኳይ የጤና አገልግሎት ሥራዎች ላይ የመሳተፍ መብትና የመተባበር ግዴታ አለባቸው።

፫ የአስቸኳይ ጊዜ የጤና አገልግሎት ክፍያ ተገልጋይ እንዲሸፍን አይጠበቅም።

## GAFA SEETTE

## <u>ADDI ADDI WORO</u>

**23. Wodhonna Biddissa Fushshate Biilloonye**

1. Qoqqowu Gashshooti Amaale Mini konne lallawa gumulsiisate wodho fushshanno.
2. Biiro lallawu jeefishira kaa’litanno tittirshu biddissuwa fushshitanno.

**24. Halamate Gadacho**

Ayee manchino konni lallawi jeefishira halamate gadacho noosi.

**25. Jeefishshu Nookki Seeranna Asoote**

Konne lallawi ledo kiphi yaano seeri, wodho, biddissunna rosamino assooti konni lallawi hanqafantino hajubba lainohunni jeefishshu dinonsa.

**26. Lallawu Kaajjanno Yanna**

Kuni lallawi Dotteessa 15/2013 M.D hanafe kaajjinoha ikkanno.

**Hawaasa, Dotteessa 15, 2013 M.D**

**Desta Ledamo**

**Sidaamu Dagoomu Qoqqowi Mootimma Pirezidaanticha**

## ክፍል ስምንት

## <u>ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች</u>

**፳፫ ደንብና መመሪያ የማውጣት ሥልጣን**

፩ የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ይህንን አዋጅ ለማስፈጸም ደንብ ያወጣል፡፡

፪ ቢሮው ለአዋጁ አፈጻጸም የሚረዱ ዝርዝር መመሪያዎችን ያወጣል፡፡

**፳፬ የመተባባር ግዴታ**

ማንኛውንም ሰው ለዚህ አዋጅ ተፈጻሚነት የመተባባር ግዴታ ይኖርበታል፡፡

**፳፭ ተፈፃሚነት የሌለው ሕግና አሰራር**

ይህንን አዋጅ የሚቃረን ሕግ፣ ደንብ፣ መመሪያ እና ልማዳዊ አሰራር በዚህ አዋጅ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት የላቸውም፡፡

**፳፮ አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ**

ይህ አዋጅ ከሚያዝያ ፲፭ ቀን ፳፻፲፫ ዓ.ም ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

**ሀዋሳ፣ ሚያዝያ ፲፭ ቀን ፳፻፲፫ ዓ.ም**

**ደስታ ሌዳሞ**

**የሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ርዕሰ መስተዳድር**